## ው ሳ ኔ

የሥር ፍ/ቤት ለውሳኔው መሠረት ያደረገው የዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል የሕክምና ሰርተፍኬት ለክሱ ምክንያት ከሆነው ጉዳይ ጋር ግንኙነት የለውም ብለናል፣

-የፌ/መ/ደ/ፍቤት በመ/ቁ.01187 ጥቅምት 13 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ኅዳር 20 ቀን 1998 ዓ.ም በመ/ቁ.26303 የሰጡዋቸው ውሳኔዎች ተሽረዋል፡፡

-መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፣

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



የሰበር መ/ቁ. 23924

የካቲት 25 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቢሲንያ ባንክ - እስክንድር ጉይተኦም ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- አበበ ከበደ (አቶ) - ጠበቃ ግርማ ሃይሌ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በስህተት ወደማይመለከተው የባንክ ሂሣብ የገባውና የተወሰደውን ገንዘብ ይመለስልኝ በማለት አመልካች ባቀረበው ክስ መነሻነት የታየውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ ለቀረበበት ክስ የመከላከያ መልስ ከመስጠቱም በተጨማሪ በበኩሉም ከሂሣቡ ያለአግባብ ወጥቶ ተወስዶአል ያለውን ገንዘብ ይከፈለው ዘንድ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርቦአል፡፡ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከመረመረ በኂላ፣ አመልካች ያቀረበውን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎአል፣ ተጠሪ ያቀረበውን ክስ ግን የተቀበለው ሲሆን፣ በዚህ መሠረትም አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍል ወስኖአል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔውን አጽንቶአል፣ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም አመልካች መጋቢት 11 ቀን 1998 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በተጠሪው የባንክ ሂሣብ ውስጥ በስህተት ገባ የተባለውን ገንዘብ ተጠሪ ሊመልስ አይገባም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ

ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተከፈተውን መዝገብ (ቁ. 144) አስቀርበን ተመልክተናል፡፡ በዚህ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው አመልካች ካቀረባቸው ማስረጃዎች መሃል ተጠሪ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ሲከፍት የሞላው ቁጥር 003 እንደነበር፣ እና አቶ ዮሐንስ ክፍሌ የተባሉት ደግሞ ልዩ የቁጠባ ሂሣብ ቁጥር 003 መክፈታቸውን፣ አቶ ሚካኤል ስዩም የተባለ ሰው በእነ አቶ ዮሐንስ ክፍሌ ልዩ የቁጠባ ሂሣብ ብር 29,417.00 ያስገባበት የጥሬ ገንዘብ ማስገቢያ ቅጽ እና የባንኩ ገንዘብ ያዥ ገንዘቡን ለመቀበሉ የፈረመበትና ማህተም ያደረገበት ደረሰኝ፣ ከዚህ በኋላ ተጠሪ በተለያዩ ጊዜአት ገንዘብ ወጪ አድርጎ መውሰዱን የሚያሳዩ ቼኮች እና የባንኩ ዋና ተቆጣጣሪ ለባንኩ ዋና ሥራ አስኪያጅና የቦርዱ ሊቀመንበር ያቀረበው ማስታወሻ እንደሚገኙ ከመዝገቡ አረጋግጠናል፡፡ ተጠሪም ባቀረበው መልስ ገንዘቡን ሊመልስ እንደማይገባ በመግለጽ የተከራከረ ቢሆንም፤ በማስረጃ ረገድ ግን የተባለውን ገንዘብ በትክክለኛ መንገድ ወደ እሱ የገባ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ በመከላከያ ማስረጃነት የጠቀሳቸው በባንኩ ተንቀሳቃሽ ሂሣብ መክፈቱን፣ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያለው የተመዘገበ ነጋዴ መሆኑ እና ባንኩ (አመልካች) በሂሣቡ ውስጥ ብር 32,951.00 እንዳለው አረጋግጦ ጽፎለት የነበረ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

እንደምንመለከተው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ገንዘብ ብር 29,417.00 ባንክ እንዲገባ ያዘዘው አቶ ሚካኤል ስዩም በእነ አቶ ዮሐንስ ክፍሌ ስም በተከፈተው ልዩ የቁጠባ ሂሣብ እንዲገባ እንጂ በተጠሪ ስም በተከፈተው ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ውስጥ እንዲገባ አላዘዘም፡፡ በእርግጥ ይህ ገንዘብ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በእነ አቶ ዮሐንስ ክፍሌ ስም በተከፈተው ልዩ ሂሣብ መግባት ሲገባው የባንኩ ሠራተኛ በፈጸመው ስህተት የተነሣ በተጠሪ ስም በተከፈተው ተንቀሳቃሽ ሂሣብ ውስጥ እንዲገባ ስለመደረጉ አመልካች በክሱ ገልጾአል፡፡ በኋላ በባንኩ ዋና ተቆጣጣሪ በተደረገው ማጣራትም ገንዘቡ በስህተት ወደማይገባው ሂሣብ ቁጥር ገብቶ መገኘቱ ታውቆአል፡፡ በመሆኑም እዚህ ላይ ሊነሳና መልስም ሊያገኝ የሚገባው ዋናው ጥያቄ አመልካች እንደክሱ ለማስረዳት አቅርቦ ካሰማው ማስረጃ ውጪ ምን የተለየ ማስረጃ እንዲያቀርብ ይጠበቅበት ነበር? የሚለው ነው፡፡ በበኩላችን እንደምናየው አመልካች የጉዳዩን አነሳስና ሂደት በትክክል የሚያሳዩ ማስረጃዎችን አቅርቦአል፡፡ ማስረጃዎቹ ሚዛን ውስጥ ገብተው ቅለታቸውና እና ክብደታቸው ሊታይ ይችል የነበረው ተጠሪ ገንዘቡ ከተባለው ወጪ በሆነ ሁኔታ ማለትም በትክክለኛ መንገድ ወደ ሂሣቡ የገባ መሆኑ የሚያሳዩ ማስረጃ አቅርቦ ቢሆን ነበር፡፡ ከክርክሩ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው እንኳንስ መከላከያ ማስረጃ ሊያቀረብ ቀርቶ ገንዘቡ ወደ ሂሣቡ ከየት በኩል እንደገባለት እንኳን ሊገልጽ አልቻለም፡፡ ይህም ማለት የማስረዳት ሸክሙን ያልተወጣው ወይም መከላከል ያልቻለው ተጠሪ ነው ማለት ነው፡፡ ሁኔታው ይህ በሆነ ጊዜም አመልካች እንደክሱ አላስረዳም ከሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ የሚያስችል የሕግ ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 00144 ታሕሣሥ 29 ቀን 1996 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27479 ጥር 10 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ ያለአግባብ የወሰደውን ብር 29,417 (ሃያ ዘጠኝ ሺህ አራት መቶ አስራ ሰባት ብር) ክሱ ከቀረበበት ሚያዝያ 30 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ ተከፍሎ እስከ ድረስ 9% (ዘጠኝ በመቶ) በመጨመር ለአመልካች ይክፈል ብለናል፡፡